የሰ/መ/ቁ. 63741

ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- አቶ መሐመድ ሰይድ አሊ - ጠበቃ እሸቱ ዓሊ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - በሌሉበት የሚታይ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪፑብሊክ ወንጀል ህግ አንቀጽ 27 እና 593ን በመተላለፍ በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊያንን ወደ ውጪ አገር ለመላክ መሞከር ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ አመልካችም ፍርድ ቤት ቀርበው የአቃቤ ሕግ የክስ ቻርጅ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሲጠየቁ የወንጀል ድርጊቱን መፈፀማቸውን በዝርዝር በማመናቸው በእምነታቸው መሠረት በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበበት አንቀጽ ሥር ጥፋተኛ ተብለውና የቅጣት አስተያየት ቀርቦ ከተመዘገበ በኋላ በቅጣት መመሪያው መሠረት በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት እና በብር 100 (አንድ መቶ) እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ብቻ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195 /2/መ/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ታህሳስ 25 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው መሠረታዊ ይዘትም አመልካች ድርጊቱን እንደአመኑ ተደርጎ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ተጠሪ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመለኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን ቅሬታ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ሲታዘዝ ከተያዘው ጭብጥ ከድርጊቱ

አፈፃፀም እንዲሁም አመልካች ላይ ከተጣለው የቅጣት መጠን አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት ኢትዮጵያዊያኑን ከሕግ ውጪ ወደ ውጭ አገር ሊልኩ ሲሉ ተይዘዋል በሚል ሲሆን ይህንኑ ደርጊት መፈፀማቸውን በዝርዝር አምነዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ድርጊቱን በዝርዝር ማመናቸውን መሠረት በማድረግም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 134/1/ መሠረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጠቷል፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት ጉዳዩን በዝርዝር ማመናቸው ተረጋግጦ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በእምነቱ መሠረት በሚሰጠው የቅጣት ውሳኔ ሕጋዊነት ላይ ይግባኝ ማለት ከሚቻል በስተቀር በእምነት መሠረት በሚሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሊቀርብ የማይችል ስለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 185/1/ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል ፡፡ አመልካች ይህንኑ በመገንዘብም ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲያቀርቡ በስር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ ይግባኝ አለማቅረባቸውን በሰበር አበቱታቸው በግልጽ የገለፁት ከመሆኑም በላይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ይህንኑ በሚገባ ይረጋገጣል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጠር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት የተሰጠው ስልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ፍርድ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖር ማረም ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ ያቀረቡት ቅሬታ የእምነት ቃላቸው በዝርዝር የተሰጠ ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤት ከተመዘገበው ይዘት ውጪ በመሆኑና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ካለው ሥልጣን አንፃር ሲታይ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ በሕጉ አተገባበርና በውጤት ደረጃ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2/መ/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ